* የማዕከሉ የተለያዩ መመሪያዎች ከስትራቴጂያዊ ሰነድ ጋር በተቻለ መጠን እንዲጣጣሙ (ተመጋጋቢ እንዲሆኑ) ተደርጓል፣

* በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የመደገፉን አሰራር በማጠናከር ተጨማሪ ሶፍትዌሮች እንዲዘጋጁ ተደርጓል፣

* የባለድርሻ አካላት ሚና ተለይቶ ተግባራዊ መሆን ጀምሯል፣

* በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሠራተኞች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር መረጃ ለመለዋወጥ የሚያስችሉ የግንኙነት መስመሮች ተግባራዊ መሆን ጀምረዋል፣

* የደንበኞችን አስተያየት መሰብሰብ የሚቻልባቸው የተለያዩ አሰራሮችም ተግባራዊ ሆነዋል፣

* በማዕከሉ ዌብሳይትና ብሮሸር በመታገዝም የግንዛቤ ማስጨበጫው ጥረት እንዲጠናከር ተደርጓል፣

* የተጀመረው ጥረት ዘለቄታነት እንዲኖረው የሚያስችሉ ስትራቴጅዎችም ተግባራዊ ሆነዋል።

## 6. እናስታውስ

* በትንሹ የሚጀመር ሙስና እያደገ አገራዊ ልማትን እና እድገትን እስከ ማደናቀፍ እና መግታት ይደርሳል!

* በህብረት ሙስናን ለማስቆም የሚያስችል አቅም አለን !

* የተሻለ ማህበረሰብን ለመፍጠር ሙስናን መዋጋት (መከላከል) የግድ ነው!

**የተከበራችሁ የኤግዚቢሽን ማዕከል ሠራተኞች፣ ደንበኞች እና ባለድርሻ አካላት፡-**

የማዕከሉን የሙስና መከላከል ስትራቴጅያዊ ሰነድን መሠረት አድርጐ ከተዘጋጀው ከዚህ ቡሮሸር የተወሰኑ መሠረታዊ መረጃዎችን እንዳገኛችሁ ይታመናል። ሰፊው አገራዊ ዓላማ እንደተጠበቀ ሆኖ ከድርጅታችን አኳያ የተቀመጠው ዓላማ "የኤግዚቢሽን ማዕከልን አሰራር ከሙስና በመከላከል፤ ዘለቄታዊ ዕድገቱን ማረጋገጥ ነው።" ስለሆነም ለዚህ የጋራ ዓላማችን እና ተጠቃሚነታችን በሚመቻችሁ መልኩ አስተያየቶችን እና ጥቆማዎችን በመስጠት መልካም ተሞክሮ የተመዘገበበትን የአጋርነት አሰራር ይበልጥ እንድታጠናክሩ በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን።


**የግንኙነት አማራጮች**

ስልክ: (251-11) 515 60 45
ሞባይል: (251-91) 121 09 99
ፋክስ: (251- 11) 553- 88 38
ኢሜል: tamrapartnership@yahoo.com
ዌብሳይት: www:/aaexhibitioncenter.com


# ኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ድርጅት



**ሙስናን መከላከል (መዋጋት) ማለት የተሻለ ህብረተሰብ መገንባት ነው!**

የዚህ ብሮሽር ዓላማ ስለ ሙስና ምንነት የተወሰነ መሠረታዊ ግንዛቤዎችን በመፍጠር በጋራ እንድንከላከለው (እንድንዋጋው) ጥሪ ማስተላለፍ ነው:: ምክንያቱም ሙስና የድርጅታችንን ብሎም የሀገራችንን ሁለንተናዊ ዕድገት የሚገታ ከመሆኑም በላይ በእያንዳንዱ ዜጋ ሕይወት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከባድ በመሆኑ ነው::

## 1. ሙስና ምንድ ነው?

የሙስና ቃል መሠረቱ “ራምፐር” የሚባል የላቲን ቃል ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙም “ማቋረጥ” ወይም “ማስተጓጎል” ማለት ነው:: የሙስና ትርጉም እንደየሀገሩ ባህል እና ተጨባጭ ሁኔታዎች በተወሰነ መልኩም ቢሆን ስለሚለያይ አንድ ወጥ የሆነ ፍች መስጠት ያስቸግራል:: ይሁን እንጂ በመሠረታዊ ሀሣቡ መግባባት ስለሚቻል እንደ ኤግዚቢሽን ማዕከል የሚከተለውን ትርጉም ሰጥተናል:-

“ሙስና ሥነ-ምግባር የጎደለው አፍራሽ (ጉጅ) ድርጊት ሲሆን በቢዝነስ፣ በማህበራዊ ህይወት እና በፖለቲካ ጉዳዩች ላይ በአብዛኛው ስውር በሆነ መልኩ እየተከሰተ ከፍተኛ ጥፋት የሚያደርስ ብልሹ አሰራር ነው:: የአሰራር ግልጽነት፣ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት፣ የጋራ አመለካከትን መሰረት ያደረገ የቡድን መንፈስ እና ተገቢ ግንዛቤ አለመኖር ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው:: የጉዳቱ መጠንም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የሚደርስ ከመሆኑም በላይ ከአድሎአዊ አሠራር ጋር የተገናኙ ችግሮችም ተጠቃሽ ናቸው:: የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት እንደ ኤግዚቢሽን ማዕከል ባሉ ድርጅቶች እድገትና የዕለት ተዕለት የሥራ አፈጻጸም ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ውስብስብ በመሆኑ በጋራ ልንከላከል ይገባል::

## 2. ሙስናን ለምን እንከላከላለን?

ሙስና “በሕዝብ እና በኢኮኖሚ” ላይ የሚያደርሰው ጉዳት በመጠንም ሆነ በአይነት ከፍተኛ ነው::

### ሀ. በሕዝብ ላይ የሚያደርሰው አሉታዊ ተጽዕኖ:-

- ✸ የማህበረሰቡን እሴቶች ይሸረሽራል፣ ያስወግዳል፣
- ✸ ሕብረተሰቡ (ሠራተኛው) በተቋሙ እና በመሪወቹ ላይ አመኔታ እንዳይኖረው ያደርጋል፣
- ✸ የሕብረተሰቡን ነፃነት ብቻ ሳይሆን ተጠቃሚነቱን ሁሉ ያሳጣል፣
- ✸ በተለያዩ አገልግሎቶች ላይ የጥራት መጓደልን ያሳድራል፣
- ✸ ፍትህን ያጓድላል፣ ያሳጣል::

### ለ. በኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽእኖ:-

- ✸ እድገትን እና ልማትን ያሰናክላል፣ ይገታል፣ እንዲያሽቆለቁል ያደርጋል፣
- ✸ የውጭ ኢንቨስትመንት እንዲቀንስ መሠረታዊ ምክንያት ይሆናል፣
- ✸ አገራችን ተወዳዳሪነቷን አጠናክራ ከዓለም አቀፍ ንግድ ተጠቃሚ የምትሆንበትን መልካም አጋጣሚ ሁሉ ያሳጣል፣
- ✸ የድርጅትን ብሎም የአገርን ውስን ሀብቶች በአግባቡ እንዳንጠቀም ያደርጋል፣
- ✸ በሕብረተሰቡ ዘንድ ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዳይኖር ያደርጋል፣
- ✸ ለሕገወጥ አሰራር መጠናከር መሠረታዊ ምክንያት ይሆናል፣
- ✸ በውጭ ኢንቨስተሮች እና ዓለም አቀፍ ግብይት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል:: ስለሆነም በጽናት ልንከላከለው ይገባል::

## 3. የሙስና አይነቶች

የሙስና አይነቶች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የሚተነተኑ ቢሆንም ጠቅለል ባለ መልኩ:-

- ✸ ከአስተዳደራዊ እና ከጥቃቅን ክፍያዎች ጋር የተያያዙት፣
- ✸ የሲስተም (የአሠራርን) ክፍተት እንደመልካም አጋጣሚ በመቁጠር ተቀናጅተው የሚከናወኑትን እና
- ✸ ድርጅት ከድርጅት ጋር በመመሳጠር የሚፈጸሙትን ከፍተኛ የሙስና ድርጊቶች ሁሉ ያካትታል::

## 4. ሙስናን ለመከላከል የሚያስችሉ 4 መሠረታዊ ስትራቴጅች

ሀ. የበላይ አመራር ቁርጠኝነት፣
ለ. ግልጽ የአሰራር ስልቶች እና መመሪያዎች፣
ሐ. የመረጃ መለዋወጫ ስልቶች፣ እና
መ. ቀጣይነት ያለው ጥረት መኖር ናቸው::

## 5. ሙስናን ከመከላከል አኳያ የኤግዚቢሽን ማዕከል ጥረትና ተሞክሮ

- ✸ የበላይ አመራሩ የሙስና መከላከል ስትራቴጅያዊ ሰነድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል፣
- ✸ ለስትራቴጅያዊ ሰነድ ትግበራ የሚመለከታቸውን የሥራ ክፍሎች ያካተተ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራ ጀምሯል:: እራሱን የቻለ ኦፊሰርም ተመድቦለታል፣
- ✸ በማዕከሉ መዋቅር ውስጥ ያሉ የሥራ ክፍሎች ቁልፍ ተግባር እና ዝርዝር ተግባራትን ያካተተ ፊዚካል ዕቅድ አዘጋጅተው የመደበኛ ሥራዎቻቸው አካል አድርገውታል፣